# ዴሞክራሲያዊ ምርጫ በኢትዮጵያ ማካሄድ ይቻላልን?

**ከሃብሮማይ** 07/15/09 (ghabrom@yahoo.com )

በአንድ አገር የዴሞክራሲ መስፈን ጉዳይ ወሳኝ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ ዴሞክራሲ በሰፈነባቸው አገሮች ህዝቦች ይመራናል የሚሉትንና የፈለጉትን ነፃ ሆነው ይመርጣሉ፡፡ህዝቦች የዴሞክራሲያዊ መብታቸውን ተጠቅመው የፈለጉትን ለመምረጥ ደግሞ አማራጮች ሊኖራቸው ያስፈልጋል ፡፡አንድ አገር አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ብቻ ካላት ምርጫ ብታካሂድም የሚያሸንፍ ብቻ እንጂ የሚሸነፍ አይኖርም ፡፡

ዴሞክራሲ ለመገንባት ምርጫ ዋነኛ ቢሆንም በምርጫው ላይ የሚወዳደሩ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች መኖራቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡በዴሞክራሲ ስርዓት የሚመሩ አገሮች የተለያዩ ፍላጎት ያላቸው ግለሰቦችም ሆነ ቡድኖች ተደራጅተው ፓርቲ በመመስረት ለአገራቸው ይጠቅማል ብለው ያሰቡትን አማራጭ ፖሊሲ ለህዝቡ በማቅረብ በፖለቲካ ጨዋታው ላይ ገብተው ይሳተፋሉ ፡፡ በምርጫ ውድድር ወቅትም በምክንያታዊነት ላይ የተመሰረተ ሞቅ ያለ ክርክር ሲያካሄዱ ይስተዋላሉ፡፡ህዝቡም ባለው ተጨባጭና ትክክለኛ መረጃ ተመርኩዞ ይጠቅመኛል ያለውን ፓርቲ ይመርጣል፡፡

ይህን ጽሁፍ ለመጻፍ ያስገደደኝ የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቭዥን ድርጅት ሰሞኑን በገዢው ፓርቲና በተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል "በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክና ምህዳር እየሰፋ ነው ወይስ እየጠበበ?" በሚል ርእስ ያዘጋጀው የውይይት መድረክ ነው ፡፡ ይህ መድረክ ፓርቲዎቹ ሃሳባቸውንና እምነታቸውን ለህዝብ ግልፅ እንዲያደርጉ፣ ህዝቡም ከቀረበው መረጃ ተነስቶ በጉዳዩ ላይ ያለውን ግንዛቤ እንዲያሳድግ የረዳ የውይይት መድረክ ነው፡፡መድረኩ በአገራችን የፖለቲካ ምህዳሩ ያለበትን ሁኔታ እንድንገነዘብ ጠቧል ወይም ሰፍቷል በሚለው ላይም የራሳችን የሆነ ምልከታ እንዲኖረን የረዳ ነው ብዬ አስባለሁ ፡፡ እንዲህ ዓይነት የውይይት መድረክ ቀጣይነት እንዲኖረውና ህዝቡም ትክክለኛውን ግንዛቤ እንዲይዝም ተጠናክሮ መቀጠል አለበት እላለሁ፡፡

ወደነበረው ውይይት ከመግባቴ በፊት የፖለቲካ መድረክ ጠበበ ወይ ሰፋ ብለን የምንናገረው በመሰረቱ ምንና ምን ሲሟላ ወይም ሲጎድል ነው የሚል ጥያቄ ጫረብኝና እኔም ያለውን ሁኔታ ለመቃኘት ሞከርኩ፡፡ እስቲ የፖለቲካ መድረክ ሰፋትና ጥበት ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ምን እንደሚመስል እንይ!

እንደሚታወቀው መሰረታዊ የፖለቲካ መድረክ ስፋትና ጥበት የሚመዘነው ከህዝብ ተሳትፎ አኳያ መሆኑ ይታወቃል፡፡ይህ ማለት ሁሉም ህዝቦች በማህበራዊ፤ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ እኩል የመሳተፍ ዕድል ሲኖራቸው ነው፡፡ አንድን ህዝብ ከሌላ ህዝብ፤አንድን ባህል ከሌላ ባህልና አንድን ቋንቋ ከሌላ ቋንቋ እያበላለጥክ መሄድ የፖለቲካ መድረክን ለማጥበብ ዋነኛና ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ ያለው ተጨባጭ ሁኔታ ሲታይ ህዝቦች በማህበራዊ፤ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ እኩል የመሳተፍ እድል አላቸው፡፡ በህገመንግስቱ አንቀጽ 25 "ሁሉም ሰዎች በህግ ፊት እኩል ናቸው "በመካከላቸውም ማንኛውም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ "በህግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል፡፡" በዚህ ረገድ በዘር፤ በብሄርብሄረሰብ ፤ በቀለም፤በፆታ፤በቋንቃ፤በሃይማኖት፤በፖለቲካ፤በማህበራዊ፤በሃብት፤በትውልድ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የህግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው ይላል፡፡

ከሌሎች አገሮች የዴሞክራሲ ባህሪይ በተለየ መልኩ የኢትዮጵያን የዴሞክራሲ ባህሪይ ልዩ የሚያደርገው የፖለቲካ መድረኩ እንዲሰፋ በማድረግ የማይተካ ሚና ያለው በህገ መንግስቱ አንቀጽ 8 ንኡስ አንቀጽ 3 ላይ የሰፈረው የቀጥተኛና የውክልና ዴሞክራሲ (direct and representative democracy) መከተሏ ነው፡፡የኢትዮጵያ ህዝቦች ስለ አገራቸው ልማት፤ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ጉዳዮች በተወካዮቻቸው ብቻ ሳይሆን በቀጥታም እያነሱ በስፋት እየተሳተፉ ይገኛሉ፡፡ይህ ደግሞ ህዝቦች የፈለጉትን የፖለቲካ ፓርቲ ለመምረጥ ሰፊ እድል እንዳጎናጸፋቸውና የፖለቲካ መድረኩም እንዲሰፋና ካለውም በላይ እንዲቀጥል

እድል የሚሰጥ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡የዚህ ዋነኛ መገለጫ ደግሞ አሁን በአገራችን ከ89 የማያንሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች መኖራቸው ነው፡፡
እኔ አሁን ግራ የገባኝ ነገር ታድያ የዴሞክራሲ ጣዕም መቅመስ ከጀመርን ገና ሁለት አስርት ዓመታት ባላስቆጠረንበት ሁኔታ ከላይ እንደተገለፀው በርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎች ህገ መንግስቱ በሰጣቸው መብት መደራጀታቸው እየታወቀ “የፖለቲካ መድረኩ ጠበበ” ማለት ምን የሚለት ፌሊጥ ነው ? የፖለቲካ መድረኩ ጠቧልና ሰፍቷል ለማለትስ ከዚህ የተለዩ ምን የመመዘኛ መስፈርት ኖሮ ይሆን ?

በአገራችን የህገ መንግስት የበላይነት ከተረጋገጠ ከአስራ አምስት አመታት በላይ ተቆጥሯል፡፡ከላይ የጠቀስናቸው መብቶችም የሰጠን ማንም ሳይሆን በህዝቦች ተሳትፎ እውን የሆነው ህገመንግስታችን ነው፡፡አገራችን የዴሞክራሲ ስርዓት ለመገንባት የምታካሂደው ጥረት የዜጎችንና የህዝቦቿን መሠረታዊ ዴሞክራሲያዊ መብቶች ባረጋገጠ ህገ መንግስት የሚመራ በመሆኑ የፖለቲካ መንቀሳቀሻ አድማሱን ማንም ሊያጠበው የማይችል መሆኑንም መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ይህን ፅሁፍ ለመፃፍ ወዳነሳሳኝ በኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት በኩል ወደ ተካሄደው የክርክር መድረክ ልውሰዳችሁና የፖለቲካ ተቃዋሚ ፓርቲዎች “የፖለቲካ ምህዳሩ ጠቧል” ብለው እኛን ለማስረዳት የሚያስችል በቂና ተጨባጭ መረጃ ሲያቀርቡ አልተስተዋሉም፡፡መንግስት በተለያዩ ጊዜያት ካለው የአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ለዴሞክራሲ ግንባታ አስፈላጊ ናቸው ብሎ ያመነባቸውን ሕጎች እያወጣ ነው፡፡ከነዚህ ህጎች መካከልም የፓርላማ ሕግና የምርጫ ቦርድ ሕግ ይገኙበታል፡፡እነዚህን ሕጎች ሕግ ሆነው እንዲፀድቁ በተቃዋሚ ፓርቲዎችና በገዢው ፓርቲ ሰፊ የሆነ ውይይት እንደተካሄደባቸው በክርክሩ ጊዜ ለመረዳት ችለናል፡፡ በፓርላማ ሕጉ ላይ ከሁለት ወር በላይ የፈጀ ውይይት እንደተካሄደና የተለያዩ ማስተካከያ ተደርጎበት እንደፀደቀም ሰምተናል፡፡በሌላም በኩል በምርጫ ቦርድ አባላት አሰያየም ላይ ምንም እንኳ እጩዎችን ጠቁሞ ወደ ተወካዮች ምክር ቤት የማቅረብ ስልጣን የጠቅላይ ሚንስትሩ ቢሆንም የፖለቲካው መድረኩ ይበልጥ ለማስፋት ተቃዋሚዎችም ከወገንተኝነት ነፃ ነው ብለው ያመኑትን አካል እንዲጠቁሙ ተደርጎ ተቀባይነት እንዳገኘ በክርክር መድረኩ

መሰማቴ በጣም አስደስተኛል፡፡ ታድያ እንዲህ ከሆነ የፖለቲካ ምህዳሩ ጠቧል ኧረ እንዴውም ተዳፍኗል ብለው የሚደሰኩሩልን ጉዳይ ያለውንና በተጨባጭ የሚታዬውን ሐቅ የሚያቀጭጭና ውሸትን የሚያጎላ አካሄድ ሆኖ እናገኛዋለን ፡፡

ከፖለቲካ ተቃዋሚ መሪዎች አንዱ ስለ ፖለቲካ ምህዳሩ መስፋት ሲናገሩ "የፖለቲካ ምህዳሩ እየሰፋ ያለው ገዢው ፓርቲ ስለፈለገ ሳይሆን እኛ ተቃዋሚዎችም ጫና ስላደረግንበት ነው" ብለዋል፡፡የፖለቲካ ተቃዋሚዎች ዛሬ ተወያይተውና ተማምነው ያፀደቁትን ሕግ ነገ ሲቃወሙት ፤ ትናንት በኛ ጫና የፖለቲካ ምህዳሩ ሰፍቷል ብለው የተናገሩትን ዛሬ የፖለቲካ ምህዳሩ ጠቧል እንዲያውም ተዳፍኗል ሲሉን ትናንት ያሉትን ዛሬ ሆን ብለው እየረሱ መሆናቸውን እንድገነዘብ አስችሎኛል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ትኩረቴን የሳበው ተቃዋሚዎች ያላቸውን ጥያቄ ለጠቅላይ ሚንስትሩ የሚያቀርቡበትና ጠቅላይ ሚኒስትሩም ምላሽ የሚሰጡበት የጥያቄ ስአት ( Question hour ) በፓርላማ መመቻቸቱና ተቃዋሚዎችም የፈለጓቸውን ጥያቄዎች የሚያነሱበት "የተቃዋሚዎች ቀን" በፓርላማ መሰየሙ ነው ፡፡ ይህ ዝግጅት ደግሞ በሬድዮና ቴሌቪዥን በቀጥታ ስርጭት ሲተላለፍ የቆዬ ነው፡፡ ይህን ዕድል ተቃዋሚዎች ያላቸውን አማራጭ ፖሊሲ ለህዝቡ ለማቅረብ ፤ገዢው ፓርቲ ያለበትን ድክመት ለማሳየት የሚችሉበትና ህዝቡም አጠቃላይ መረጃውን የሚከታተልበትና ግንዛቤ የሚወስድበት ጭምር ነው፡፡ይህ አካሄድ ደግሞ የፖለቲካ ምህዳሩን ይበልጥ ያሰፋ ነው፡፡ይሁን እንጂ አብዛኛው የፖለቲካ ተቃዋሚዎች ይህንን ዕድል ሲጠቀሙበት አልታዩም፡፡ ያለውን የፖለቲካ መድረክ በአግባቡ ሳይጠቀሙ ሌላ ዓይነት የፖለቲካ መድረክ መፈለግ ህዝብን ለመምራት ዝግጅት ካለው የፖለቲካ ፓርቲ የሚጠበቅ አይመስለኝም፡፡ለነገሩ በምርጫ '97 ተቃዋሚዎች የአዲስ አበባ ወንበሮችን ሙሉ በሙሉ አሸንፈውም እኮ ባገኙት ዕድል አልተጠቀሙበትም ፡፡ ያገኙትን መጠቀም ሲገባቸው ላላገኙት በመቋመጥ አይደል እንዴ የመረጣቸውን ህዝብ አንገት ያስደፉት !

አሁንም ከነበራቸው አካሄድ የተማሩ አይመስሉም፡፡በተገኘው ሰፊ የፖለቲካ ምህዳር መንቀሳቀስ ሲገባቸው ልክ በምርጫ ’97 እንዳደረጉት ሁሉ ሕገ መንግስታዊውን ስርአት በመናድ በነውጥና በሁከት ስልጣን ካልተቆጣጠርን ብለው የመረጣቸውን የአዲስ አበባን ህዝብ እንዳሳፈሩ ሁሉ አሁንም ያለውን ሰፊ የፖለቲካ ምህዳር ሳይጠቀሙ የቀደመውን አካሄድ የመረጡ ይመስላሉ ፡፡ ይህ አካሄድ ደግሞ ለማንም እንደማይጠቅም ህዝቡን በሚገባ አውቋልና ባለው የፖለቲካ ምህዳር መንቀሳቀስ ይሻላል እላለሁ፡፡

ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት ሕገ መንግስቱ ህዝቡ በቀጥታ በራሱ ጉዳይ ወሳኝ ላይ ተሳታፊ እንዲሆን በማድረግ የፖለቲካ መድረኩን እንዲሰፋ አድርጎታል፡፡ የፖለቲካ መድረኩ ጠቧል እያሉ በተደጋጋሚ የሚለፍፉት በህገ ወጥ መንገድ የሚንቀሳቀሱትና ህጋዊውና ህገወጥነትን እያጣቀሱ ለመራመድ የሚሞክሩት ናቸውና፡፡ እነርሱ መንገዳቸውን አስተካክለው በጠራና ሰላማዊ መንገድ ቢጓዙ ለእነርሱም፣ ለአገርም ለህዝብም ጠቃሚ ነው እላለሁ ፡፡ በህግ የበላይነት በሚመራ አገር መሆን ያለበት ብቸኛው መስመርም ይሄ በመሆኑ፡፡

ሕግና ስርዓቱን አክብረው የሚንቀሳቀሱ ወገኖች ዛሬ ሁሉ በአገራችን ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ማካሄድ እንደሚቻል ተገንዝበው በስፋት ለመንቀሳቀስ ሙከራ እያደረጉ ናቸው፡፡መንግስትም በሕጋዊና ሕገመንግስታዊ አካሄድ ወደ ውድድር የሚገቡ ፓርቲዎች ከግማሽ መንገድ በላይ ተጉዞ እንደሚያበረታታቸው እያስገነዘባቸው ነው ፡፡ይሁን እንጂ በአገራችን ካለው ሕግና ስርዓት ውጭ መንቀሳቀስ የሚፈልጉ፣ ሕግ በወጣ ቁጥር አናርኪዝምን የሚያቀነቅኑ፣ በመሰረታዊ የዴሞክራሲ ስርዓቱ አጋር መሆን ሲገባቸው የመጪውን የ2002 ምርጫ ዴሞክራሲያዊ እንዳይሆን በተለያዩ ኤምባሲዎች በር በመቆም የሚያንኳኩ እንዳሉ መካድ አይቻልም፡፡ ለእነዚህ ሃይሎች የምለው ጉዳይ ቢኖር የአገሪቷ ባለቤት የሆነው ህዝብ ዴሞክራሲያዊ የሆነ ምርጫ ተካሂዶለት የራሱን ወኪሎች መምረጥ ይፈልጋልና እባካችሁ እንቅፋት አትሁኑበት ፡፡

የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ የፖለቲካ መድረኩ ያጠባል ብለው የሚያስቡ ግለሰቦችና ቡድኖች መገንዘብ ያለባቸውም በአገራችን አሁን በተጨባጭ ህገመንግስትን አክብረው የሚንቀሳቀሱ ሁሉ በህገመንግስቱ በተደነገገው መሰረት የፖለቲካ መድረኩ ከአሁን በበለጠ እንደሚሰፋ ፀሐይ የሞቀው የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡ስለሆነም በሕግና ስርዓት ለሚመራ ማንኛውም ፓርቲ የሚቀጥለውን ምርጫ ዴሞክራሲያዊ እንደሚሆን ማንም የሚገነዘበው ነው ፡፡ይሁን እንጂ ህገ ወጥነትን ለማስፋፋት ለሚሞክሩ ግን ሁኔታው ይህን የሚያስተናግድ አይሆንም ፡፡

ህዝቡም የሚቀጥለው ምርጫ የአገራችን የዴሞክራሲ ግንባታ አጋር መሆን ያቃታቸው ቡድኖች የሁከት መድረክ መሆን እንደማይችል በማያሻማ መልኩ ተገንዝቧልና ሕግና ስርዓትን ተከተሉ ብዬ ምክሬን እለግሳችሁዋለሁ፡፡ህጋዊነትንና ህገወጥነትን እያጣቀሱ የሚሄዱ ሃይሎች የህግ የበላይነትን ሲመች የሚቀበሉት ሳይመች ሲቀር የሚሸሩት እንደማይሆን ሲያውቁት የፖለቲካ መድረኩ እንደ መርፌ ቀዳዳ ሊጠብባቸው እንደሚችል እገነዘባለሁ ፡፡እነዚህ ህገ ወጦች መላወሻ ሲያጡና የህግ የበላይነት ሲያስገድዳቸው ወደ ህጋዊና የህግ የበላይነትን የተረጋገጠበት ሰፊ የፖለቲካ መድረክ ይገባሉም ብዬ እገምታለሁ፡፡የአገራችን ዴሞክራሲ ግንባታ ጥላሸት ለመቀባትና ሕጋዊና ሕገወጥ አካሄዶችን እያጣቀሱ ለመጓዝ ለመረጡ ፓርቲዎች በአገራችን ሕጋዊ በሆነው ሰፊ የፖለቲካ ምህዳር ተንቀሳቀሱ እላለሁ ፡፡ በመጪው 2002 በአገራችን ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ማካሄድ እንደሚቻል መንግስት በማያሻማ መልኩ አስቀምጧል፡፡የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅትም ይህንን የውይይት መድረክ ቀጣይ በማድረግ ተግቶ መስራት እንዳለበት በዚህ አጋጣሚ ልጠቁም እወዳለሁ ፡፡

ሰላም!